www.abyssinialaw.com

# የተሻሻለው የ1995 ዓ.ም

## የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ

ታህሳስ 9/1995 ዓ.ም

ጋ ም ቤ ላ

www.abyssinialaw.com

አዋጅ ቁጥር 27/1995

# በ1995 ዓ/ም የተሻሻለዉ የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ

በክልሉ ነዋሪ ሕዝብ በሰፊዉና በዝርዝር ተመክሮበት እስከ አሁን በሥራ ላይ የቆየዉን ሕገ-መንግሥት አሁን በተጨባጭ እየታየ ባለዉ አጠቃላይ ሁኔታ የክልል መንግሥት አካላትን የሥልጣን ክፍፍልና ተጠያቂነት በግልፅ በሚያሣይ መልኩ ማሻሻሉ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ በሥራ ላይ ያለዉ የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 100 መሠረት ይህ የተሻሻለዉ የ1994 ዓ.ም የክልሉ ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ታዉጇል፡፡

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የተሻሻለዉ የ1995 ዓ.ም የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 27/1995 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. በ1995 ዓ/ም የተሻሻለዉ የ1995 ዓ.ም ሕገ መንግሥት ስለመጽደቁ

በአዋጅ ቁጥር 2/1988 የፀደቀዉ የክልሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ በስፋት ከታየ በኋላ በ1995 ዓ.ም ተብሎ ተሻሽሎ የወጣዉ የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊመንግሥት ሕገ መንግሥት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

3. ስለ ነባር ሕጎች ተፈፃሚነት

በሥራ ላይ ያለ ማንኛዉም ነባር ሕግ ከተሻሻለዉ ሕገ መንግሥት ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ የተሻሻለዉ ሕገ መንግሥት ከዛሬ ታህሳስ 9 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጋምቤላ ታህሳስ 9 ቀን 1995 ዓ.ም
ኦኬሎ ኝጌሎ
የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል ፕሬዚዳንት

www.abyssinialaw.com

# የተሻሻለዉ የ1995 ዓ/ም የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት

## መግቢያ

እኛ የጋምቤላ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሀገራችንና በክልላችን ተንሰራፍቶ የቆየዉን የጭቆና ሥርዓት ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችንን አፍኖ በተዛቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች በመከተል ለድህነትና ለኋላቀርነት ዳርጐን መቆየቱ በማያዳግም ሁኔታ መታረም ያለበት መሆኑን በማመን የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን በነፃ ፍላጐታችን በክልላችን የሕግ የበላይነት ለማክበርና ለማስከበር ባለን ጽኑ እምነት ላይ በመመርኮዝ ክልላችንን በጋራ ለመገንባት የግለሰብን የብሔረሰቦችን ሃይማኖቶች ጠቃሚ ባህሎችና ልምዶች ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸዉ እንዲራመዱ ዓላማችን በመሆኑ፣

የክልላችንን ሕዝቦች ለረጅም ዓመታት አብረዉና ተሳስረዉ የኖሩና ይህን አብሮ የመኖር ባህልና ልምድ በማጐልበት ለልማታችንና ለእድገታችን በጋራ በጠንካራ መሠረት ላይ በመቆም ወደ ተሻለ የእድገት ጐዳና እንድንመራ ፅኑ እምነት ያለን በመሆኑ፣

እኛ የአኝዋ፣ የኑዌር፣ የመዠንግር፣ የኦፖና ኮሞ ብሔረሰቦች ለተፋጠነ ኢኮኖሚ ዕድገት ለዘላቂ ሠላምና ዲሞክራሲ የምንበቃዉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክን ሕገ መንግሥት መሠረት ያደረገና የክልላችንን ተጨባጭ ሁኔታዎች ያገናዘበ የክልላችን ሕገ መንግሥት ሲኖረን መሆኑን በውል በመረዳት፣

እስከ አሁን በሥራ ላይ ያለዉን የ1988 ዓ.ም ሕገ መንግሥታችንን አሁን በተጨባጭ እየታየ ባለዉ ሀገራዊ ሁኔታና ክልላዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ግልጽ አሠራርን የሚከተል ለመረጠው ሕዝብ ተጠያቂ የሆነና ብቃት ያለዉ መንግሥታዊ አደረጃጀትን በሚያመላክት መልኩ አግባብ ያሉ ጥልቅ እይታ ተደርጐበት ተሻሽሎ መዉጣት ያለበት መሆኑን በማመን፣

እነሆ ዛሬ ታህሳስ 9 ቀን 1995 ዓ.ም በጋምቤላ ከተማ ባካሄደዉ የክልሉ ምክር ቤት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ የቀረበዉን የተሻሻለ የክልሉ ሕገ መንግሥት መክረንና በዝርዝር ተወያይተን በሙሉ ድምጽ አጽድቀናል።

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1

### የክልሉ መንግሥት ስያሜ

ይህ ሕገ መንግሥት የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የሚቋቋመዉ መንግሥት " የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት " በሚል ስም ይጠራል፡፡

### አንቀጽ 2

### የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ክልል ወሰን

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 1/8 በተደነገገዉ መሠረት የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል ተብሎ የተጠቀሰዉ ነዉ፡፡ በዚህ መሠረት በምሥራቅ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል፣ በደቡብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ ከሱዳን ሪፐብሊክ በሰሜን ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት፤ በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ከደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጋር የሚዋሰነዉ መልክዓ ምድር ነዉ፡፡

### አንቀጽ 3

### ሰንደቅ ዓላማ

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማ ከላይ ቀይ፣ከመሐል ነጭና አረንጓዴ፣ ከታች ጥቁር ሆኖ በነጩ ቀለም መሐል ጥቁር ኮከብ ምልክት ያለዉ ነዉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ 4

### የክልሉ መንግሥት ዓርማ

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዓርማ በመሐሉ የበቆሎ እሸት፣ በስተቀኝ የተሰቀለ ባህላዊ ከበሮ፣ በስተግራ ዓሣ ያለበት ሆኖ ዙሪያዉ በጥብጣብ የተያዘ የዘንባባ ዝንጣፊዎችን የያዘ ነዉ፡፡ ትርጉሙም በሕግ ይወሰናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 5
## የክልሉ ብሔራዊ መዝሙር

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል የራሱ የሆነ ብሔራዊ መዝሙር ይኖረዋል:: የክልሉ መዝሙር የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎችና የክልሉን ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ አብሮ ለመኖር ያላቸዉን እምነት እንዲሁም የወደፊት የጋራ ዕድላቸዉን የሚያንፀባርቅ ሆኖ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 6
## ስለ ቋንቋ

1. የክልሉ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል::

2. እንደየብሔረሰቡ ቋንቋዉ የተለያየ ይሁን እንጂ የክልሉ ቋንቋዎች ሁሉ በክልሉ ሕገ መንግሥት እኩል እዉቅና ይኖራቸዋል::

3. የክልሉ ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸዉና በፈለጉት ቋንቋ የመማር መብት አላቸዉ

4 በክልሉ የሚገኙ ሕዝቦች በአማርኛ የመማር መብት አላቸዉ::

## አንቀጽ 7
## ርዕሰ ከተማ

የክልሉ ርዕሰ ከተማ ጋምቤላ ነዉ:: ዝርዝሩ በቻርተር ይደነገጋል::

## አንቀጽ 8
## የጾታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ መንግሥት ዉስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገዉ የሴቷንም ጾታ ያካትታል::

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ሁለት
## የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች
### አንቀጽ 9
### የሕዝቡ ወሣኝነት

1. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ሕዝብ የክልሉ ብሔራዊ መንግሥት የበላይነት ሥልጣን ባለቤት ናቸዉ።

2. የሕዝቡ የበላይነት የሚገለፀዉ በሚመርጣቸዉ ተወካዮችና ራሱ በቀጥታ በሚያደርገዉ ዲሞክራሲያዊ ተሣትፎ ነዉ።

### አንቀጽ 10
### የሕገ መንግሥቱ የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. ይህ ሕገ መንግሥት የብሔራዊ ክልሉ የበላይ ሕግ ነዉ። ማንኛዉም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የማንኛዉም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ዉሣኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረዉም።

2. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግሥት አካል የፖለቲካ ድርጅትና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸዉ ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸዉ።

3. በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገዉ ዉጭ በማንኛዉም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነዉ።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 11
## ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰዉ ልጅ በተፈጥሮ የሚመነጭ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸዉ::

2. የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸዉ::

## አንቀጽ 12
## የመንግሥትና ሐይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸዉ::
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም::
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም:: ሃይማኖት በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም::

## አንቀጽ 13
## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልዕ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት::

2. ሕዝቡ በመረጠዉ ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታዉ ሊያነሳዉ ይችላል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

3. ማንኛዉም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል በሕግ ተጠያቂ ይሆናል::

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ሶስት

## መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

### አንቀጽ 14

### ተፈጻሚነትና አተረጓገም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው።
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጐማል

## ክፍል አንድ

## ሰብዓዊ መብቶች

### አንቀጽ 15

### የሕይወት፣የአካል ደህንነትና ነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና ነፃነት መብት አለው።

### አንቀጽ 16

### በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

### አንቀጽ 17

### የአካል ደህንነት መብት

www.abyssinialaw.com

ማንኛዉም ሰዉ በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለዉ፡፡

## አንቀጽ 18

## የነፃነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ማንኛዉም ሰዉ ነፃነቱን አያጣም፡፡
2. ማንኛዉም ሰዉ በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

## አንቀጽ 19

## ኢ- ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛዉም ሰዉ ጭካኔ ከተሞላበት ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለዉ፡፡
2. ማንኛዉም ሰዉ በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም፡፡ ለማንኛዉም ዓላማ በሰዉ የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነዉ፡፡
3. ማንኛዉም ሰዉ በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛዉም ሥራ እንዲሰራ ማድረግ የተከለከለ ነዉ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት የሚለዉ ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፡፡

   ሀ/ ማንኛዉም እሥረኛ በእሥር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሰራ የተወሰነዉን ወይም በገደብ ከእሥር ከተለቀቀበት ጊዜ የሚሰራዉን ማንኛዉንም ሥራ፣

   ለ/ ማንኛዉም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናዉ የማይፈቅድለት ሰዉ በምትክ የሚሰጠዉ አገልግሎት፣

   ሐ/ የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛዉም አገልግሎት፣

www.abyssinialaw.com

መ/ በሚመለከተዉ ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢዉ የሚፈፀመዉን ማንኛዉንም የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ሥራ፣

## አንቀጽ 20
## የተያዘ ሰዉ መብት

1. ወንጀል ፈጽሟል በመባል የተያዘ ሰዉ የቀረበበት ክስና ምክንያት በዝርዝርና ወዲያዉኑ በሚገባዉ ቋንቋ እንዲነገረዉ መብት አለዉ።

2. የተያዘ ሰዉ ላለመናገር መብት አለዉ። የሚሰጠዉ ማንኛዉም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለዉ ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያዉኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጠዉ መብት አለዉ።

3. የተያዘ ሰዉ በአርባ ስምንት ሰዓታት ዉስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለዉ። ሆኖም ይህ የጊዜ ገደብ ሰዉዬዉ ከተያዘበት ቦታ ወደ አቅራቢያዉ ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለዉ ግምት የጠይቀዉን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያዉኑ ፍ/ቤት እንደቀረበም በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽለት መብት አለዉ።

4. የያዘዉ አካል /ፖሊስ/ ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደቡ መሠረት ፍርድ ቤት በማቅረብ ግለሰቡ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለዉ። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታዉ የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘዉ ሰዉ በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠይቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቀድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገዉን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት ምርመራዉን አጣርተዉ የተያዘዉ ሰዉ በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለዉን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት።

5. የተያዘ ሰዉ በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸዉም ማስረጃ እንዲያምን አይገደድም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረዉም።

www.abyssinialaw.com

6. የተያዘ ሰዉ በዋስ የመፈታት መብት አለዉ፡፡ ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱ ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታት ጭምር በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 21
## የተከሰሰ ሰዉ መብት

1. በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ ጊዜ ዉስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለዉ፡፡ የተከራካሪዉን የግል ሕይወት፣ የሕዝቡን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡

2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንደነገረዉና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት አለዉ፡፡

3. በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለዉ፡፡

4. የተያዘ ሰዉ የቀረበበትን ማንኛዉም ማስረጃ የመመልከት የቀረበበትንም ምስክር የመጠየቅ ለመከላከል የሚያስችለዉን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙለት የመጠበቅ መብት አለዉ፡፡

5. በመረጠዉ የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣቱ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አለዉ፡፡

6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠዉ ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለዉ፡፡

7. የፍርዱ ሂደት በማይገባዉ ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምለት የመጠየቅ መብት አለዉ፡፡

## አንቀጽ 22

www.abyssinialaw.com

## በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰዉ መብት

1. በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰዉ ሰብዓዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለዉ::

2. ከትዳር ጓደኛዉ፣ ከቅርብ ዘመዶቹ ከሃይማኖት አባቶች ከአማካሪዎቹ፣ ከሐኪሞች ጋር የመገናኘትና እንዲጐበኙት ዕድል የማግኘት መብት አለዉ::

## አንቀጽ 23
## የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛዉም ሰዉ የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰተበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም:: እንዲሁም ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈፃሚ ከነበረዉ የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛዉም ሰዉ ላይ አይወሰንም::

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 1 ) ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሣሹ ወይም ለተቀጣዉ ሰዉ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣዉ ሕግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል::

## አንቀጽ 24
## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛዉም ሰዉ በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ዉሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም::

## አንቀጽ 25
## የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ በማንኛዉም ሥፍራ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ እዉቅና የማግኘት መብት አለዉ::

www.abyssinialaw.com

2. ማንኛዉም ሰዉ ሰብዓዊ ክብሩንና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለዉ::

3. ማንኛዉም ሰዉ የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጐች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሣደግ መብት አለዉ::

## አንቀጽ 26
## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸዉ:: በመካከላቸዉ ማንኛዉም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል:: በዚህ ረገድ በዘር፣ ብሔር ብሔረሰብ፣ በቀለም በጾታ፣ በቋንቋ ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ በሀብት በትዉልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸዉ::

## አንቀጽ 27
## የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ የግል ሕይወቱና ግላዊነቱ የመከበር መብት አለዉ:: ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰዉነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታዉ ያለ ንብረት የመጠበቅ መብት ያጠቃልላል::

2. ማንኛዉም ሰዉ በግል የሚፈጽማቸዉና የሚፃፋቸዉ፣ በፖስታ የሚልካቸዉ ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸዉ ግንኙነቶች አይደፈሩም::

3. የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸዉ:: አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን የሕዝብን ሠላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ሕጐች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 28
## የሐይማኖትና የእምነት ነፃነት

1. ማንኛዉም ሰዉ የማሰብ፣ የእምነትና የሐይማኖት ነፃነት አለዉ:: ይህ መብት ማንኛዉም ሰዉ የመረጠዉ ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ የሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል::

2. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 122 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰ እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸዉን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችላቸዉ የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማትን ለማቋቋም ይችላሉ::

3. ማንኛዉም ሰዉ የሚፈልገዉን እምነት ለመያዝ ያለዉን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም::

4. ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸዉ መሠረት የሐይማኖታቸዉንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸዉን የማሣደግ መብት አላቸዉ::

5. ሃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለዉ የሕዝብን ደህንነት፣ ሠላም ጤና፣ ትምህርት የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶች ነፃነቶችና መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል::

## አንቀጽ 29
## በስብዕና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰዉ ልጅ ላይ የተፈፀመዉ ወንጀሎች ተብለዉ የተወሰኑትን ወንጀሎች፣ የሰዉ ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመዉሰድ በአስገዳጅነት ሰዉን የመሰወር ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ

www.abyssinialaw.com

አይታገድም። በሕግ አዉጭው ክፍልም ሆነ በማንኛዉም የመንግሥት አካል ዉሣኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም።

## ክፍል ሁለት

## ዲሞክራሲያዊ መብቶች

### አንቀጽ 30

### የአመለካከት እና ሃሣብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለዉን አመለካከት መያዝ ይችላል።

2. ማንኛዉም ሰዉ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሣቡን የመግለጽ ነፃነት አለዉ። ይህ ነፃነት በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕይወት በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠዉ በማንኛዉም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛዉንም ዓይነት መረጃና ሃሣብ የመሰብሰብ፣ የመቀበል የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።

3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፣

   ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛዉም መልክ የተከለከለ መሆኑን፣

   ለ/ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን፣

4. ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሃሣቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸዉን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረዉ የሕግ ጠበቃ ይደረግለታል።

5. በክልሉ መንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ

www.abyssinialaw.com

መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለዉ ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል::

6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸዉ የሚችለዉ የሃሣብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለዉ አስተሳሰባዊ ዉጤት ሊገታ አይገባዉም በሚል መርህ ላይ ተመስርተዉ በሚወጡ ሕጐች ብቻ ይሆናል:: የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰዉን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ሥርዓቶች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ:: የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ የሚከለከሉ ይሆናሉ::

7. ማንኛዉም ዜጋ ከላይ ለተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦች ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል::

## አንቀጽ 31

## የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሠላም የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዉ:: ከቤት ዉጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሠላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸዉ ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሠላማዊ ሠልፍ ሠላምን፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥስ ለማስጠበቅ አግባብነት ያላቸዉ ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ::

2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት የሰዉን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጐች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም::

## አንቀጽ 32

## የመደራጀት መብት

www.abyssinialaw.com

ማንኛዉም ሰዉ ለማንኛዉም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለዉ። ሆኖም አግባብ ያለዉን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 33

## የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ በክልሉ ዉስጥ የሚገኝ ሰዉ በመረጠው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ ሠርቶ የመኖር፣ ሀብትና ንብረት የማፍራት፣ የመያዝ እንዲሁም በፈለገ ጊዜ ከክልሉ የመዉጣት መብት አለዉ።

## አንቀጽ 34

## የመሥራት መብት

የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያዉቅ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በማንኛዉም የክልሉ መንግሥታዊ ሥራዎች ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ የመሥራት መብት አለዉ።

## አንቀጽ 35

## የጋብቻ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነዉ የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር ብሔረሰብ፣ በሃይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸዉ የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸዉ። በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸዉ። በፍቺ ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ የሕግ ድንጋጌዎች ይወጣሉ።

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሰረታል።

3. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነዉ። ስለሆነም ከሕብረተሰቡና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለዉ።

www.abyssinialaw.com

4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረዉ መሠረት በሃይማኖት፣ በባህልና በሕግ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተዉ ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እዉቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል፡፡

5. ይህ ሕገ መንግሥት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጐች መሠረት ማዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 36
## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ሕገ-መንግሥት በአረጋገጣቸዉ መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸዉ፡፡

2. ሴቶች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገዉ መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸዉ፡፡

3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸዉ ምክንያት የደረሰባቸዉን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ይኸዉ የታሪክ ጠባሳ እንዲታረምላቸዉ በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸዉ፡፡ በዚህ ረገድ የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚዊ እንዲሁም በመንግሥትና በግል ተቋሞች ዉስጥ ሴቶች ከወንዶች በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሣታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነዉ፡፡

4. ሴቶች ከጐጂ ልማድ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸዉን መብት መንግሥት ማስከበር አለበት፡፡ ሴቶችን የሚጨቁኑና በአካላቸዉ ወይም በአዕምሮአቸዉ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጐች፣ ወጐችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸዉ፡፡

5. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ ዕድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸዉ፡፡

6. በመንግሥት መ/ቤቶች ወይም በግል ድርጅት ተቀጥረዉ የሚሰሩ ሴቶች፣

www.abyssinialaw.com

ሀ/ የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ዉስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል፡፡

ለ/ የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነዉ መሠረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድ ሊጨምር ይችላል፡፡

7. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸዉን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸዉን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃና አቅም የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡

8. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸዉ፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ የማስተላለፍ፣ የማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸዉ፡፡ እንዲሁም ዉርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸዉ፡፡

9. ሴቶች በብሔራዊ ክልሉ የልማት ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸዉን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸዉ፡፡

## አንቀጽ 37
## የሕፃናት መብት

1. ማንኛዉም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፡፡

ሀ/ በሕይወት የመኖር፣

ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ሐ/ ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸዉን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

www.abyssinialaw.com

መ/ ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ፣ በጤናዉና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣

ሠ/ በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ዉስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፣

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ከመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አዉጭ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት::

3. ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በማቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግሥት ወይም የግል አጋለማዉታን ተቋሞች የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተዉ መያዝ አለባቸዉ::

4. ከጋብቻ ዉጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕፃናት እኩል መብት አላቸዉ::

5. መንግሥት ለአጋለማዉታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል:: በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸዉንና ትምህርታቸዉን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ ያበረታታል::

## አንቀጽ 38
## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ::

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ ዉሣኔ ወይም ፍርድ፣

www.abyssinialaw.com

ሀ/ ማንኛዉም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

ለ/ ማንኛዉም ቡድን ወይም ተመሣሣይ ጥቅም ያላቸዉን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠበቅና የማግኘት መብት አለዉ።

## አንቀጽ 39
## የጋምቤላ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች

የጋምቤላ ብሄር ብሄረሰቦችና ብሔራዊ ክልል ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያ ሪፐብልክ መንግሥት የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለዉ መብቱ በማናቸዉም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነዉ። በዚህም መሠረት የብሔራዊ ክልሉ ሕዝብ፣

1 የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርፁንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ እንዲሁም በቋንቋዉ የመጠቀም፣ ቋንቋዉን የማሳደግ፣ ባህሉን የመግለጽ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለዉ።

2 በራሱ መልክዓ ምድራዊ ክልል ዉስጥ የራሱን ዕድል በራሱ የመጨረስ፣ ራሱን በራሱ የማስተዳደርና እንዲሁም በፌዴራሉ መንግሥት ዉስጥ በነፃነት፣ እድልዎ በሌለበት ተገቢና ፍትሃዊ በሆነ የዉክልና አግባብ ዉጤታማ ተሣትፎ የማድረግ መብት አለዉ።

3 የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል መንግሥቱ አስተዳደሮች ዉስጥ ሚዛናዊ ዉክልና የማግኘት መብት አለዉ።

4 በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ ተረገጡ ወይም ተሸራረፉ ብሎ ባመነበትና አነኝህንም በአንድነት ሥር ሆኖ ሊያስተካክላቸዉ ባልቻለበት ጊዜ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 በተደነገገዉ መሠረት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ ተግባራዊ ያደርጋል።

www.abyssinialaw.com

5. የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለዉ መብት በሥራ ላይ የሚዉለዉ፣

ሀ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በክልል ምክር ቤቱ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣

ለ/ የክልሉ ምክር ቤት የመገንጠል ዉሣኔዉ በደረሰበት በሶስት ዓመታት ጊዜ ዉስጥ የፌዴራሉ መንግሥት ሕዝበ ዉሣኔ ሲያደራጅ፣

ሐ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝብ ዉሣኔዉ በአብላጫዉ ድምጽ ሲደገፍ፣

መ/ የፌዴራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለመረጠዉ ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብና፣

ሠ/ በሕግ በሚወሰነዉ መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነዉ።

6. በዚህ ሕገ መንግሥት ዉስጥ ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ማለት ቀጥሎ የተገለፁትን ባህሪያት የሚያሳይ ማህበረሰብ ነዉ። ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሣሣይ ልምዶች ያላቸዉ፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸዉ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልዉና አለን ብለዉ የሚያምኑና የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸዉና በአብዛኛዉ በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸዉ።

## አንቀጽ 40
## የንብረት መብት

1. በክልሉ ዉስጥና ዉጭ የሚኖር ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል። ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረት የመሸጥ፣ የማዉረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።

2. ለዚህ አንቀጽ አላማ የግል ንብረት ማለት በክልሉ ዉስጥና ከክልሉ ዉጭ የሚኖር ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ወይም ሕጋዊ ሰዉነት በሕግ የተሰጣቸዉ አገር

www.abyssinialaw.com

አቀፍ ወይም ክልላዊ ማህበራት ወይም አግባብ ባላቸዉ ሁኔታዎች በሕግ በተለይ በጋራ የንብረት ባለቤቶች እንዲሆኑ የተፈቀደላቸዉ ማህበረሰቦች፣ በጉልበታቸዉ፣ በፈጠራ ችሎታቸዉ ወይም በካፒታላቸዉ የአፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረዉ ዋጋ ያለዉ ዉጤት ነዉ፡፡

3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነዉ፡፡መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ የሕዝብ የጋራ ንብረት ነዉ፡፡

4. የክልሉ አረሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለመፈናቀል መብታቸዉ የተከበረ ነዉ፡፡ አፈፃፀሙ በሕግ ይወሰናል፡፡

5. በክልሉ የሚገኙ አርብቶ- አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸዉ ያለመፈናቀል መብት አላቸዉ፡፡ አፈፃፀሙ በሕግ ይወሰናል፡፡

6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸዉን ያስከብርላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

7. በክልሉ ዉስጥና ከክልሉ ዉጭ የሚኖር ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ የሚገነባዉ ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገዉ ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለዉ፡፡ ይህም መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማዉረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ደግሞ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብቶችን ያካትታል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመዉሰድ ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 41

## የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. የክልሉ ነዋሪ የሆነ ወይም በክልሉ ዉስጥ ለመኖር የሚፈልግ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በክልሉ ዉስጥ በማንኛዉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያዉ የመረጠዉን ሥራ የመሥራት መብት አለዉ።

2. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያዉን፣ ሥራዉንና ሙያዉን የመምረጥ መብት አለዉ።

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸዉ።

4. የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜዉ እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።

5. የክልሉ መንግሥት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደዉ ደረጃ እንክብካቤ ያደርል።

6. የክልሉ መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፣ እንዲሁም በሚያካሄደ የሥራ ዘርፍ ዉስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።

7. የክልሉ መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸዉ እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

8. ገበሬዎች እና አርብቶ - አደሮች በየጊዜዉ እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸዉንና ለብሔራዊ ሀብት ካደረጉት የምርት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ዉጤታቸዉ የማግኘት መብት አላቸዉ። የክልሉ መንግሥት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት።

www.abyssinialaw.com

9. የክልሉ መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 42
## የሠራተኞች መብት

1. የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸዉ የሚፈቅድላቸዉ የመንግሥት ሠራተኞች፡-

   ሀ/ የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸዉ፡፡ ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት ከአሰሪዎችና ጥቅማቸዉን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብቶች ያካትታል፡፡

   ለ/ ከዚህ በላይ ንዑስ አንቀጽ ሥር የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታ ለማሰማት መብት አላቸዉ፡፡

   ሐ/ ከፍ ብሎ በፊደል ተራ ቁጥሮች ሀ እና ለ መሠረት እዉቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ፡፡

   መ/ ሴት ሠራተኞችለተመሣሣይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ፡፡

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ በየጊዜዉ ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀናት ደመወዝ የሚከፈልባቸዉ የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡

3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እዉቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት

www.abyssinialaw.com

የሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋል፡፡

## አንቀጽ 43
## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታዎችን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማገኘት መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ፡፡

2. የክልሉ ነዋሪዎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ በሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ፕሮጀክቶች ላይ ሃሣባቸዉን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸዉ፡፡

3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጐቶች ማሟላት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 44
## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸዉ፡፡

2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሄዳቸዉ ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸዉ የተነካባቸዉ ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ አራት

## የክልሉ መንግሥት አወቃቀር

### አንቀጽ 45

### የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. የክልሉ መንግሥት በክልል፣ በብሔረሰብ ዞኖች፣ በአስተዳደራዊ ወረዳዎችና በቀበሌዎች የተዋቀረ ነዉ:: ይሁን እንጂ የክልሉ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ሌሎች የአስተዳደር እርከኖች ሊያዋቅርና ሥልጣናቸዉን በሕግ ሊወስን ይችላል::

2. በክልሉ ዉስጥ የሚቋቋሙት የአስተዳደር እርከኖች በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ ላይ በመመሥረት ይሆናል::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ከተሞች ልማታቸዉን የሚያፋጥን የራሳቸዉ አስተዳደር ይኖራቸዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

### አንቀጽ 46

### የክልሉ መንግሥት አባላት

1. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መሥራች አባላት የሚከተሉት ብሔር ብሔረሰቦች ናቸዉ::

    1. የአኙዋ ብሔረሰብ
    2. የኑዌር ብሔረሰብ
    3. የመዠንግር ብሔረሰብ
    4. የኦፖ ብሔረሰብ
    5. የኮሞ ብሔረሰብ

www.abyssinialaw.com

2. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል አባላት እኩል መብትና ሥልጣን አላቸዉ።

3. በእያንዳንዱ የብሔረሰብ ዞን በራስ አስተዳደር ዉስጥ የሚገኙ ሌሎች አናሳ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የየራሳቸዉን ቀበሌዎች በራስ የማስተዳደር መብት ይጠበቃል፣ በክልልና በዞን በቀጥታ የመወከል መብትም ይጨምራል።

## አንቀጽ 47
## የአስተዳደር እርከኖች የአከላለል ለዉጦች

1. የአስተዳደር እርከኖች ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩ በሚመለከታቸዉ የአስተዳደር እርከኖች ስምምነት ይፈጽማል። የሚመለከታቸዉ አካላት መስማማት ካልቻሉ ጉዳዩ የሚመለከተዉ የብሔረሰብ ምክር ቤት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፣ የክልሉ ምክር ቤት የዚሁ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ይወስናል።

2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ 1 መሠረት የቀረበዉ ጉዳይ ከ3 ወር ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ በክልል ምክር ቤት የመጨረሻ ዉሣኔ ይሰጥበታል።

## ምዕራፍ አምስት
## የክልሉ መንግሥት ሥልጣን አወቃቀር እና ክፍፍል

## አንቀጽ 48
## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ መንግሥት ሕግ አዉጪ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለወከለዉ ሕዝብ ነዉ።

2. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተደድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነዉ።

www.abyssinialaw.com

3. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻነዉ፡፡

## አንቀጽ 49

## የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብልክ ሕገ መንግሥት ዉስጥ በዉል ተለይተዉ ለፌዴራሉ መንግሥት ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሉ በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ዉጭ ያለ ማናቸዉም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር ይሆናል፡፡

2. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊ መንግሥቱ፡-

2.1 የክልሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣

2.2 የክልሉ ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጐችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣

2.3 የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣዉ ሕግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፡፡

2.4 ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብልክ ሕገ መንግሥትንና ይህንን ሕገ መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል፣

2.5 የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞችአስተደደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህንኑ በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ዉስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

2.6 የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣

www.abyssinialaw.com

2.7 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ በሕግ መሠረት ምህረት ያደርጋል::

2.8 ለክልሉ በተወሰነዉ የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ የክልሉን በጀት ያወጣል፣

2.9 በክልል መስተዳድሩና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

2.10 የመሬት መጠቀሚያ ክፍያን ይወስናል፣

2.11 የእርሻ ሥራ ገቢ ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

2.12 በክልሉ ዉስጥ በግል ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል፣

2.13 በክልል መስተደድሩ ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብርና የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

2.14 ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር:-

ሀ/ በጋራ ከሚያቋቁሟቸዉ የልማት ድርጅቶች የሚገኘዉን የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክሶችን በሕጉ መሠረት ይከፍላል፣

ለ/ ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ከባለአኪሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክሶችን በሕጉ መሠረት ይካፈላል፣

ሐ/ ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማናቸዉም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘዉን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በሕጉ መሠረት ይካፈላል፣

2.15 በክልል መስተዳድሩ አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚነጩ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል፣

2.16 ከደን የሚገኘዉ የሮያሊቲ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

www.abyssinialaw.com

2.17 በክልሉ ዉስጥ ማናቸዉም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አዉጥቶ በሥራ ላይ ያዉላል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለ ክልሉ ምክር ቤት

### አንቀጽ 50

### ስለ ክልሉ ምክር ቤት አባላት

1. የክልሉ ምክር ቤት አባላት ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በምስጢር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ፡፡

2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ዉስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ፡፡ የተለየ ዉክልና እንደሚያስፈልጋቸዉ የታመነባቸዉ አናሳ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን በምርጫ ምክር ቤቱ ዉስጥ ይወከላሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

3. የምክር ቤቱ አባላት የመላዉ የክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ናቸዉ፡፡ ተገዥነታቸዉም፡-

   ሀ/ ለሕገ መንግሥቱ
   
   ለ/ ለመረጣቸዉ ሕዝብ
   
   ሐ/ ለራሳቸዉ ሕሊና ብቻ ይሆናል፡፡

4. ማንኛዉም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ዉስጥ በሚሰጠዉ ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡

5. ማንኛዉም የክልል ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም በወንጀል አይከሰስም፡፡

www.abyssinialaw.com

6. ማንኛዉም የምክር ቤት አባል የመረጠዉን ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል

7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ድንጋጌ እንደአግባብነቱ በየደረጃዉ በሚገኙ ምክር ቤቶች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፣

## አንቀጽ 51
## የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የክልል ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የክልሉ ሕግ አዉጭ አካል ነዉ።

2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በብሔራዊ ክልሉ የዉስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ነዉ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ሥር የሰፈረዉ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

   3.1 በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የፌዴራሉን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጐችን የማይፃረሩ ልዩ ልዩ ሕጐችን ያወጣል።

   3.2 የሕዝቡን ብዛት፣ የክልሉን ስፋትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ግምት ዉስጥ በማስገባት በክልሉ ዉስጥ ተጨማሪ የአስተዳደር እርከኖችን ወይም የራስ በራስ አስተዳደሪዊ አካባቢዎችን ያቋቁማል።

   3.3 የክልሉ ብሄረሰቦችን በመወከል በፌዴሬሽን ም/ቤት የሚሳተፉትን በቀጥታ በሕዝብ ባልተመረጡበት ጊዜ ከክልሉ ም/ቤት አባላት መርጦ ይልካል።

www.abyssinialaw.com

3.4 የፌዴራሉ መንግሥት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጐራባች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጋር የሚደረጉ ስምምነቶችን ያፀድቃል::

3.5 የራሱን አፈ ጉባኤ ይመርጣል፣ ለምክር ቤቱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይሰይማል፣

3.6 ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድሩን በምርጫ ይሰይማል፣ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል::

3.7 በርዕሰ መስተደድሩ አቅራቢነት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት፣ ም/ፕሬዚዳንት ፣ዋና ኦዲተሩንና ምክትል ዋና ኦዲተሩን ይሾማል::

3.8 የክልሉን ጠቅላይ፣ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ያቋቁማል፣ ዳኞችን ይሾማል፣

3.9 የኦዲትና ሌሎች የቁጥጥር አካላቱን ያቋቁማል፣

3.10 በሕጉ መሠረት ምህረት ያደርጋል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሉን ያቋቁማል፣

3.11 የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች ያፀድቃል፣

3.12 የክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ሕጐችን ያወጣል፣ የክልሉን በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣

3.13 ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት፣ ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠንናለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል::

3.14 ለክልሉ መንግሥት በተከለለዉ የገቢ ምንጭ በክልሉ ዉስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል፣

www.abyssinialaw.com

3.15 የክልል መስተዳድሩን የሠራተኛ አስተዳደር የሥራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፣

3.16 በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2/17/ ሥር ለክልሉ መንግሥት በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል፣

3.17 የሀገሪቱንና የክልሉን ሕግጋተ መንግሥታት አዋጆችና ሌሎች ሕጐችን በክልሉ ዉስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ደንቦች ያወጣል፣

3.18 የክልሉን ርዕሰ መስተደድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣

3.19 ለብሄረሰብ ዞኖችና ለአስተዳደራዊ እርከኖች የሕዝብ ብዛትን ዋነኛ መመዘኛ ባደረገ ቀመር በጀት ይመድባል፡፡

## አንቀጽ 52
## የፖለቲካ ሥልጣን

1. በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ያደራጃል፣ ወይም ያደራጃሉ፣ ይመራል ወይም ይመራሉ፣

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደየአግባብነቱ ለብሔረሰብ ዞን፣ለብሔረሰብ ልዩ ወረዳ፣ ለወረዳ እና ለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 53
## ስለ ክልሉ ምክር ቤት ጽ/ቤት

1. የክልሉ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል፡፡
2. የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 54
## ስለ ምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. አብላጫ መቀመጫ ባገኙት የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3/5 መሠረት ከም/ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነዉ::

2. አፈ ጉባኤዉ የሥራ ዘመን የክልሉ ም/ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል::

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ለብሔረሰብ ዞን፣ ለብሔረሰብ ልዩ ወረዳ፣ ለወረዳና ለቀበሌ ምክር ቤቶች አፈ ጉባኤዎች ያገለግላሉ::

## አንቀጽ 55
## የአፈ ጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ም/ቤት አፈ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል::
ይኖሩታል::

1. የም/ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል፣ ይመራል፣

2. ም/ቤቱን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፣

3. የም/ቤቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣

4. ም/ቤቱ በአባሎቹ ላይ እንዲወሰድ የወሰነዉን የዲስፒሊን እርምጃ ያስፈጽማል፣

5. የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያስተባብራል፣

www.abyssinialaw.com

6. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል::

## አንቀጽ 56

## የምክትል አፈ ጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር

ምክትል አፈ ጉባኤዉ ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤና ለክልሉ ም/ቤት ሆኖ:-

1. በአፈ ጉባኤዉ ተለይተዉ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል፣
2. አፈ ጉባኤዉ በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል::

## አንቀጽ 57

## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል::
2. ከምክር ቤቱ አባላት ዉስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባዉ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::

   የምክር ቤቱ ዉሣኔ በስብሰባ ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል::

3. የክልል ምክር ቤት አባላት የሚመረጡ ለአምስት ዓመታት ነዉ:: የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል:: የቀድሞዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ጊዜ ዉስጥ አዲሱ ም/ቤት ሥራዉን ይጀምራል::
4. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባኤዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል:: የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛዉ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባኤዉ የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት::

www.abyssinialaw.com

5. የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፣ ሆኖም ስብሰባዉ በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ወይም በክልሉ አስፈፃሚ አካል ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄዉን ከደገፉት ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል::

### አንቀጽ 58

### የምክር ቤቱ ዉሣኔዎችና ዉስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓቶች

1. በዚህ ሕገ መንግሥት ዉስጥ ተገልጾ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸዉም ዉሣኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ነዉ::

2. ምክር ቤቱ ዉስጣዊ አሠራሩንና የሕግ አወጣጡን ሂደት አስመልክቶ ዝርዝር ደንቦችን ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያዉል ይችላል::

## ምዕራፍ ሰባት

## የሕግ አስፈፃሚ አካል

### አንቀጽ 59

### የአስፈሚነት ሥልጣን

1. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠዉ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነዉ::

2. ርዕሰ መስተደድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸዉ ለክልሉ ምክር ቤት ነዉ::

3. የክልሉ መስተደድር ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸዉ በጋራ ለሚሰጡት ዉሣኔ ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 60

## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፣ የአስፈፃሚ ቢሮዎች ኃላፊዎችና በሕግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው።

2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ርዕሰ መስተደድሩ ነው።

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ነው።

4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወስነው ውሣኔ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል።

## አንቀጽ 61

## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በክልሉ ምክር ቤትና በፌዴራሉ መንግሥት የወጡ ሕጐችና የተላለፉ ውሣኔዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ መተርጐማቸውን ያረጋግጣል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል፣

2. የክልል መስተዳድሩ አስፈጻሚ አካላት የሌሎች ተቋማት አደረጃጀት ይወስናል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣

3. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3.2 ድንጋጌዎች ሥር ለክልሉ ም/ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚቀርቡ የሽግሽግ ጥያቄዎችን አጣርቶ ይወስናል፣

www.abyssinialaw.com

4. የክልሉን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፣

5. የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎች ይነድፋል፣ የሕግ ረቂቆችን ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፣ የተወሰነዉንም ያስፈጽማል፣

6. በክልሉ ዉስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፣

7. የክልሉ ምክር ቤት በሚሰጠዉ ሥልጣን መሠረት ደንቦችንና መመሪያዎችን ያወጣል፣

8. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያዉጃል፣ በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገዉ የጊዜ ወሰን ዉስጥ የታወጀዉን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል::

9. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3.16 ሥር ለክልሉ ምክር ቤት አስቀድሞ የተሰጠዉ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ ሊሰበሰብ ባልቻለበት ሁኔታ የጤና ችግርና ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ በክልሉ ዉስጥ በሚደርስበት ጊዜ አስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አዉጥቶ በሥራ ላይ ያዉላል::

10. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል::

## አንቀጽ 62

## የርዕሰ መስተደድሩ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በክልሉ ምክር ቤት ዉስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል::

2. በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕሰ መስተዳድሩ የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነዉ::

3. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርነት ምርጫ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከፀደቀ በኋላ ሥራዉን ከመጀመሩ በፊት የጋራ ስብሰባዉ በወሰነዉ ጊዜ ስብሰባዉ ፊት ለሕገ-መንግሥቱና ለክልሉ ሕዝቦች ያለዉን ታማኝነት በሚቀጥለዉ ቃላት ይገለጻል::

www.abyssinialaw.com

« እኔ ________________ በዛሬው ዕለት የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ:: »

## አንቀጽ 63

## የርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልል መስተዳድሩ ሥራ መሪ፣ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና የክልሉ ፕሬዚዳንት ነው::

2. ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተደድሩ፣

   ሀ/ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል፣

   ለ/ የክልሉ መንግሥት ሕግ አዉጭና ሕግ አስፈፃሚ አካላት በየበኩላቸዉ መክረዉ ያፀደቋቸዉን አዋጆችና ደንቦች በጋምቤላ ነጋሪት ጋዜጣ ይታወጁ ዘንድ በአሥራ አምስት ቀናት ዉስጥ ፊርሞ ይልካል፣ በአሥራ አምስት ቀናት ዉስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይዉላል፣

   ሐ/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣቸዉን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ዉሣኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል፣

   መ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የክልሉን ዋና ኦዲተርና ምክትል ኦዲተር መርጦ ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስሾማል፣

   ሠ/ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን ጨምሮ የክልሉ መስተዳድ ም/ቤት አባላት የሚሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችን ሹመት ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል:: ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የክልል ምክር ቤት አባል መሆን አለበት::

www.abyssinialaw.com

ፈ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥሮች መ እና ሠ ሥር የሰፈረዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁኔታ ከምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በመለስ ያሉትን ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሠራል:: የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚንዳት በጊዜያዊነት የሚመደቡ ከዳኞች መካከል ይሆናል፣

ሰ/ ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ዉጭ የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎች፣ በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ያሾማል:: ምክትል የቢሮ ኃላፊዎች፣ ኮሚሽነሮችና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች መርጦ ያሾማል፣

ሸ/ የክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙት ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊሲ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ቀ/ በክልሉ የሚገኙትን የበታች አስተዳደር እርከኖች ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

በ/ የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉን ምክር ቤት መሥራች ጉባኤ ይጠራል፣

ተ/ ለክልል ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣

ቸ/ በክልል ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል::

## አንቀጽ 64
## የምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር

1. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ሹመቱ የሚፀድቅ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ/ በርዕሰ መስተዳድሩና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተለይተዉ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል፣

www.abyssinialaw.com

ለ/ ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል::

2. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነዉ::

## አንቀጽ 65

## የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በዚህ ሕገ መንግሥት የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ያስችለዉ ዘንድ የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል::

2. የርዕሰ መስተደድሩ ጽ/ቤት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽ/ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል::

3. የጽ/ቤቱ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 66

## ስለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና አስተደደራዊ ተቋማት መቋቋም

1. የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የእለት ተዕለት ሥራዎችን የሚያከናዉኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎች፣ ኮሚሽኖች፣ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ተቋማት እንደአስፈላጊነታቸዉ ይቋቋማሉ::

2. የቢሮዎች፣ የኮሚሽኖች፣ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ከፍተኛ ተቋማት ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለመስተደድር ምክር ቤቱ ይሆናል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገዉ ቢኖርም የክልሉ ቢሮዎች፣ ኮሚሽኖች፣ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ተቋማት ተጠሪነት ከተቋቋሙበት አላማና ከሚያስፈጽሙት ተልዕኮ ጋር አግባብነት ላላቸዉ የክልሉ መንግሥት የበላይ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ይሆናል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ ስምንት

## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

### አንቀጽ 67

### ስለ ነፃ ዳኝነት አካል መቋቋም

1. የክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡
2. የዳኝነትን ሥልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠዉ ተቋም ዉጪ የሚያደርግና በሕግ የተደነገገዉን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም፡፡

### አንቀጽ 67

### ስለ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የዳኝነት አካላት

በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 5 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ሕገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እዉቅና አግኝተዉ ሲሰራባቸዉ የነበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት እዉቅና አግኝተዉ ይደራጃሉ፡፡

### አንቀጽ 68

### የዳኝነት ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነዉ ፡፡
2. በየትኛዉም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸዉም የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነዉ፡፡
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸዉን በሙሉ ነፃነት ያከናዉናሉ፡፡ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡
4. ማንኛዉም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ የተወሰነዉ የጡረታ መዉጫ እድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ዉጭ ከዳኝነት ሥራዉ አይነሳም፡፡

www.abyssinialaw.com

ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲስፒሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም፣

ለ/ በሕመም ምክንያት ዳኛዉ ተግባሩን በተገቢዉ ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና፣

ሐ/ የጉባኤዉ ዉሣኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ የአብልጫ ድምጽ ሲደገፍና ሲፀድቅ::

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የሰፈሩት ድንጋጌዎች አፈፃፀም ዝርዝር በሕግ ይወሰናል::

6. የማንኛዉም ዳኛ የጡረታ መዉጫ ጊዜ አይራዘምም::

## አንቀጽ 69

## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችይደራጃል:: የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነዉ::

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣

ሀ/ ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛዉና የመጨረሻዉ የዳኝነት ሥልጣን፣

ለ/ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣንና፣

ሐ/ ማናቸዉም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠዉ የመጨረሻ ዉሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካለዉ ክልላዊ ሥልጣን በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሆን ይዳኛል::

www.abyssinialaw.com

4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠዉ ዉሣኔ ላይ የሚቀርበዉ ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል፡፡

5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠዉ ዉሣኔ ላይ የሚቀርበዉ ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል፡፡

6. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል፡፡

7. የክልሉ ፍርድ ቤቶች በዉክልና የሚፈፀሙትን ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ለማከናወን የሚያወጡትን የገንዘብ ወጪ በተመለከተ ከፌዴራል መንግሥቱ ማካካሻ እንዲሰጣቸዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 70
## ስለዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡

2. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡

3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በእጩዎቹ ላይ ያለዉን አስተያየት መጠየቅና የተሰጠዉን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀዉን አስተያየት በሶስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የእጩ ዳኞቹን ሹመት ተቀብሎ ያጸድቃል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 71

## ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም

1. በክልሉ ዉስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል::

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ጉባኤዉን በሰብሳቢነት ይመራል::

3. የጉባኤዉን አባላት ዝርዝር፣ ስብጥር ፣ ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 72

## ሕገ መንግሥቱን ስለመተርጐም

1. በክልሉ ዉስጥ የሕገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ወይም የትርጉም ጥያቄ ሲነሣ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙ ከእያንዳንዱ ብሔረሰብ ምክር ቤቶች ከአፖና ከኮሞ ጭምር ተዉጣጥቶ በዉክልና የሚሰየም የሕግ መንግሥት ትርጊሚ ኮሚሲዮን በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

2. ኮሚሲዮኑ የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ መክሮ በስልሳ ቀናት ዉስጥ ዉሣኔ ይሰጣል::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የሚቋቋመዉ ኮሚሲዮን የአገለግሎት ዘመን አባላቱ የተወከሉባቸዉ የወረዳ ምክር ቤቶች የሥራ ዘመን ሲሆን መንግሥታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ይሰበሰባል::

4. ኮሚሲዮኑ የራሱን ሰብሳቢና ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል መርጦ ሥራዉን የሚያከናዉን ሲሆን ለሥራዉ የሚያስፈልገዉን የጽሕፈት ቤት አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ከክልሉ ምክር ቤት ያገኛል::

## አንቀጽ 73

www.abyssinialaw.com

## የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡

2. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አሥራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

   ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሰብሳቢ፣

   ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ምክትል ሰብሳቢ፣

   ሐ/ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልል ምክር ቤት የሚሰየምና በሙያ ብቃታቸዉና በሥነ ምግባራቸዉ የተመሰከረላቸዉ ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፣

   መ/ በአፈ ጉባኤዉ አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም ሶስት ተወካዮች ፣

## አንቀጽ 74
## የአጣሪ ጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይህንን ሕገ መንግሥት መሠረት አድርገዉ ከክልሉ የሚመነጩ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በሚያደርገዉ ማጣራት መሠረትም የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በጉዳዩ ላይ የራሱን የዉሣኔ ሃሣብ አዘጋጅቶ ለሕገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል፡፡

2. አጣሪ ጉባኤዉ በክልሉ መንግሥት አካላት የሚወጡ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማናቸዉም ሁኔታ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተዉ ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሲቀርብለት ከመረመረና ካጣራ በኋላ የመጨረሻ ዉሣኔ ለኮሚሲዮኑ ያቀርባል፡፡

3. በፍርድ ቤቶች ዘንድ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ጉባኤዉ፣

   ሀ/ የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘዉ ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተዉ ፍርድ ቤት ወዲያዉኑ ይመልሳል፡፡ ሆኖም ባጣሪ

www.abyssinialaw.com

ጉባኤዉ ዉሣኔ ቅር የተሰኘ ማናቸዉም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታዉን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለኮሚሲዮኑ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል::

ለ/ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም አሰናድቶ ለኮሚስዮኑ ለመጨረሻ ዉሣኔ ያቀርባል::

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ስለ የብሄረሰብ አስተዳደሮች አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀጽ 75

### የብሔረሰብ አስተዳደሮች አደረጃጀት

1. በብሔራዊ አስተዳደሮች ዉስጥ የአኙዋሃ፣የኑዌርና የመዠንገር ሕዝቦች በሰፈሩባቸዉ አካባቢዎች በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር በተደነገገዉ መሠረት የብሔረሰብ አስተዳደር ተቋቁሟል፣

2. እያንዳንዱ ብሔረሰብ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል፣

ሀ/ የብሔረሰብ ምክር ቤት

ለ/ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት

ሐ/ የብሔረሰብ አስተዳደር የዳኝነት አካል

### አንቀጽ 76

### የብሔረሰብ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. እያንዳንዱ የብሔረሰብ ምክር ቤት ለክልል ምክር ቤት አባልነት የተመረጡትን ጨምሮ በዉስጡ ከታቀፉት የወረዳ ም/ቤቶች በልዩ ሁኔታ የሚመረጡ አባላት ያሉት ሆኖ ይቋቋማል::ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤፤

www.abyssinialaw.com

2. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት ለፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮችና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጣቸዉ ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔረሰብ ምክር ቤቶች የየብሔረሰባቸዉ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸዉ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ሥር የሠፈረዉ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የብሔረሰብ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የሚከተሉት ልዩ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ/ ብሔረሰቡ የሚጠቀምበትን የሥራ ቋንቋ መወሰን፣

ለ/ ብሔረሰቡ በቋንቋዉ ለመናገርና ለመጻፍ፣ ቋንቋዉን ለማሳደግ፣ለመጠበቅ፣ ለመግለጽ፣ለማዳበርና ለማስፋፋት፣እንዲሁም ታሪኩን ለመንከባከብ ያለዉን መብት ማስጠበቅ፣

ሐ/ በዚህ ሕገ-መንግሥት ዉስጥ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠዉ የሕግ አዉጭነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተደራጀበት አካባቢ ከክልል አቀፍ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር በማይጻረር ሁኔታ የራሱን ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያች አዉጥቶ በሥራ ላይ ማዋል፣

መ/ የክልሉ ምክር ቤት ያፀደቀዉን ብሔራዊ ክልላዊ ዕቅድና በጀት መሠረት በማድረግ የአካባቢዉን ዕቅድና በጀት ማዉጣትና መርምሮ ማጽደቅ፣

ሠ/ የብሔረሰብ አስተዳደሩን አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤዉንና ዋና አስተዳዳሪዉን በምርጫ መሰየም፣

ረ/ በዋና አስተዳደሪዉ የሚቀርቡለት የብሄረሰብ አስተዳደሩን ምክትል አስተዳደሪና ሌሎች የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ማጽደቅ፣

ሰ/ በብሔረሰብ አስተዳደሩ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ዳኞች ሹመት ረገድ የበኩሉን አስተያየት ለክልሉ ምክር ቤት መስጠት፣

ሸ/ የብሔረሰብ አስተዳደሩን ዋና አስተዳደሪ ጨምሮ ሌሎች የአስተዳደሩን ባለሥልጣናት ለጥያቄ መጥራትና የአስፈጻሚዉን አካል አሠራር መመርመር፣

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 77

### ስለብሔረሰብ ምክር ቤት አመራር

1. የብሔረሰብ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት ኖሮት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በሚመረጡ የራሱ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይመራል::ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

2. አፈ-ጉባኤዉንና ምክትል አፈ-ጉባኤዉን ዝርዝር ሥልጣንና ኃላፊነቶች አስመልክቶ በዚህ ሕገ-መንግሥት ስክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ የተጻፉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

3. ምክር ቤቱ ለሥራዉ እንደአስፈላጊነቱ ራሱን በልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያደራጃል፣

## አንቀጽ 78

### የብሔረሰብ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የብሔረሰብ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል::የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል:: የቀድሞዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራዉን ይጀምራል::

2. የብሔረሰብ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሶስት ጊዜ ይሰበሰባል::

3. ከምክር ቤቱ አባላት ዉስጥ ከሁለት ሶስተኛዉ በላይ የሚሆኑ በስብሰባዉ ላይ ከተገኙ የስብሰባዉ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል:: የምክር ቤቱ ዉሣኔ በስብሰባዉ ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል::

4. የብሔረሰበ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል::ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል::የብሔረሰብ አስተዳደሩ ዋና አስተዳደሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አንድ ሶስተኛዉ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቀ አፈ-ጉባኤዉ ምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 79

## ስለብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለሚመለከተዉ ብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳደሪና ለብሔረሰብ ምክር ቤት ነዉ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና ለርዕሰ መስተዳድሩ ተጨማሪ ተጠሪነት ይኖርበታል።

3. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት የብሔረሰብ አስተዳደሩ ዋና አስተዳደሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በአስተዳደሩ ዉስጥ የሚገኙ አስፈጻሚ መምሪያ ኃላፊዎች የሚካተቱበት አካል ሆኖ ይቋቋማል።

## አንቀጽጽ 80

## የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ/ በብሔረሰብ ም/ቤቱ በክልሉ ምክር ቤትና በፌደራሉ መንግሥት አካላት የወጡ ሕጐችና የተሰጡ ዉሣኔዎች በአስተዳደሩ ዉስጥ በሥራ መተርጐማቸዉን ያረጋግጣል፣

   ለ/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ አባላት የሆኑ መምሪያዎችንና ሌሎች አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ይወስናል፣ሥራቸዉን ይከታተላል፣በበላይነት ይመራል፣

   ሐ/ የአስተዳደሩን ዓመታዊ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ለብሔረሰብ ምክር ቤቱ ያቀርባል፣ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፣

   መ/ የአስተዳደሩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በዝርዝር ይነድፋል።በብሔረሰብ ምክር ቤቱ ያፀድቃል፣የተወሰነዉንም ያስፈጽማል፣

   ሠ/ በብሔረሰብ አስተዳደሩ ዉስጥ ሕገና ሥርዓት መከበሩንና የሕዝቡ ሠላምና ደህንነት መጠበቁን ያረጋግጣል፣

www.abyssinialaw.com

ረ/ በብሔረሰብ ምክር ቤቱና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፡፡

2. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸዉ በጋራ ለሚሰጡት ዉሣኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

## አንቀጽ 81

### የብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳደሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳደሪ በብሔረሰብ ም/ቤት ዉስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት/ቶች/አቅራቢነት ከብሔረሰብ ም/ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል፡፡
2. በዚህ ሕገ-መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የዋና አስተዳዳሪዉ የሥራ ዘመን የብሔረሰብ ም/ቤቱ የሥራ ዘመን ነዉ፡፡

## አንቀጽ 82

### የዋና አስተዳዳሪዉ ሥልጣንና ተግባር

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ የአስተዳደሩ ሥራ መሪ፣የአስተዳደር ም/ቤቱ ሰብሳቢና የብሔረሰብ አካባቢዉ ተጠሪ ነዉ፡፡
2. ዋና አስተዳዳሪዉ ተጠሪነቱ ለብሔረሰቡ ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ነዉ፡፡
3. ሌሎች የዋና አስተዳዳሪዉን ሥልጣንና ተግባራት በሚመለከት በዚህ ሕገ መንግሥት የርዕሰ መስተዳድሩን ሥልጣንና ተግባራት አስመልክቶ የተጻፉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸዉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 83

### የብሔረሰብ አስተዳደር ምክትል አስተዳዳሪ

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክትል አስተዳዳሪ በዋና አስተዳደሪዉ አቀራቢነት ሹመት በብሔረሰብ የሚፀድቅ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖሩታል::
   ሀ/ በዋና አስተዳዳሪዉና በብሔረሰብ አስተዳደር ም/ቤቱ ተለይተዉ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል፣
   ለ/ ዋና አስተዳዳሪዉ በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣
2. ምክትል አስተዳደሪዉ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳደሪዉና ለብሔረሰብ አስተዳዳር ም/ቤት ነዉ::

## አንቀጽ 84

### የዋና አስተዳዳሪዉ ጽ/ቤት

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል::
2. የዋና አስተዳዳሪዉ ጽ/ቤት የብሔረሰብ አስተዳዳር ም/ቤት ጽ/ቤት በመሆን ጭምር ሊያገለግል ይችላል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## ምዕራፍ አሥር

### ስለወረዳ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ 85

### አደረጃጀት

የወረዳ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል::

1. በሥሩ ከተደራጁ ቀበሌዎች በሚወከሉ የሕዝብ ተመራጮች ተዋጽኦ የሚቋቋም የወረዳ ምክር ቤት፣

www.abyssinialaw.com

2. ከዚሁ ምክር ቤት አባላት መካከል ተመርጦ በሚሰየም የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አማካኝነት፣ የሚቋቋም የአስተዳደር ም/ቤትና፣

3. በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የተቋቋመ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል፣

## አንቀጽ 86

## የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ አስተዳደር በተደራጀበት አካባቢ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት እቅዶችን ለማዘጋጀትና ለመወሰንም ሆነ የክልሉ መንግሥት እንዲሁም የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳ አካላት በየጊዜዉ የሚያወጧቸዉን ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸዉም ሥልጣን ይኖረዋል።

2. እያንዳንዱ ወረዳ እራሱን የማስተዳደር፣ አካባቢዉን የማልማትና በዉስጣዊ ጉዳዮቹ ላይ ዉሣኔ የመስጠት መብትና ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን አስተዳደር የበታች አካል ነዉ።

## አንቀጽ 87

## ስለወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥና ተጠሪነት

1. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳዉ የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ።

2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸዉ ሕዝብ ይሆናል።

## አንቀጽ 88

## የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ዉስጥ ከፍተኛዉ መንግሥታዊ የሥልጣን አካል ነዉ። ተጠሪነቱም ለዞኑ ምክር ቤት ይሆናል።

) አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ www.abyssinialaw.com
ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

የወረዳዉን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶችና፣ አስተዳደራዊ የሥራ ዕቅዶች፣ፕሮግራሞችና በጀት ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል፣ በጀት በቀመር ለቀበሌዎች ይመድባል::

በወረዳዉ ዉስጥ መሠረታዊ የግብርና የልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀዉ መካሄዳቸዉንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ መከናወኑን ይከታተላል፣

ነዋሪዉ ሕዝብ ለልማት ሥራ በስፋት የሚነሳሳበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፣

/ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ/ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አፈ ጉባኤን፣ ምክትል አፈ ጉባኤዉንና ዋና አስተዳዳሪዉን በምርጫ ይሰይማል፣ በዋና አስተዳዳሪዉ የሚቀርቡለትን ምክትል አስተዳዳሪና ሌሎች የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያፀድቃል::

የራሱን ዉስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓት መወሰኛ መመሪያ ያወጣል፣

/ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ/ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርና ሌሎች ገቢዎች ወቅቱን ጠብቀዉ መሰብሰባቸዉን ያረጋግጣል፣ ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎችን ይጥላል፣

ክልሉ ከሚመድበዉና ከሚያስተዳድረዉ ዉጭ ያለዉንና የወረዳዉን የገቢ ምንጭ ይጠቀማል፣

የፌዴራሉና የክልሉ ሕግጋተ መንግሥታትና ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነዉ የወረዳዉን ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ አዉጥቶ በሥራ ላይ ያዉላል፣

የወረዳዉን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች የወረዳዉን ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈፃሚዉን አካል አሠራር ይመረምራል::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 89
## ስለ ምክር ቤቱ አመራርና አፈ-ጉባኤ

1. የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት እንዲኖረዉ ሆኖ ከአባላቱ መካከል ተመርጠዉ በሚሰየሙ አፈ ጉባኤ እና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

2. አፈ ጉባኤዉ ተጠሪነቱ ለወረዳዉ ም/ቤት ሆኖ ወቅቱን ጠብቆ ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራትና ጉባኤዉን የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል፣

3. ሌሎች የአፈ ጉባኤዉ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች የክልል ምክር ቤቱን አፈ ጉባኤ አስመልክቶ በዚህ ሕገ መንግሥት የተደነገጉት እንደየአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## አንቀጽ 90
## የወረዳ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ

ምክትል አፈ ጉባኤዉ ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤና ለወረዳዉ ም/ቤት ሆኖ፣

1. በአፈ ጉባኤዉ ተለይተዉ የሚሰጡት ተግባራት ያከናዉናል::

2. አፈ ጉባኤዉ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል::

## አንቀጽ 91
## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የወረዳ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል፣

2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል:: የምክር ቤቱ ዉሣኔ በስብሰባ ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል፣

www.abyssinialaw.com

3. የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡ የቀድሞዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ጊዜ ዉስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራዉን ይጀምራል፡፡

4. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል፡፡ ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባኤዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ ከም/ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤዉ የምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ 92</u>
## <u>ስለ ወረዳዉ አስተዳደር ምክር ቤት</u>

1. የወረዳዉ አስተዳደር ምክር ቤት የተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪና ለወረዳዉ ምክር ቤት ነዉ፣

2. የወረዳዉ አስተዳደር ምክር ቤት የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ እንዲሁም በወረዳዉ ዉስጥ የተቋቋሙ ዋና ዋና ዓላማ አስፈፃሚ የሴክተር ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚገኙበት አካል ሲሆን ከወረዳዉ ምክር ቤት በተጨማሪ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ተጠሪነት ይኖረዋል፡፡

## <u>አንቀጽ 93</u>
## <u>ስለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የወረዳ አስተዳዳር ምክር ቤት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡
   ሀ/ የፌዴራሉና የክልሉ መንግሥታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች ደንቦች፣ መመሪያዎች እቅዶችና ፕሮግራሞች በተቋቋመበት ወረዳ ዉስጥ በሥራ ላይ እንዲዉል ያደርጋል፣

www.abyssinialaw.com

ለ/ በወረዳዉ ዉስጥ የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በበላይነት ያስተባብራል፣ ሥራቸዉን ይከታተላል፣ ይመራል፣

ሐ/ በሕግ መሠረት የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እና ሌሎች ገቢዎችን ይሰበስባል፤ ተጨማሪ ገቢዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ አጥንቶ ለወረዳዉ ምክር ቤት ለዉሣኔ ያቀርባል፡፡

መ/ የወረዳዉ ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለወረዳዉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፣

ሠ/ የወረዳዉ ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣ የወረዳዉን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል፣ ሥራቸዉን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

ረ/ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳዉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ሰ/ ሕዝቡን ለልማት ሥራ በስፋት ያነሳሳል፣ የገጠር ልማትን ያፋጥናል፣ የተፈጥሮ ሀብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል፣

ሸ/ በወረዳ ዉስጥ የሚገኝ ማንኛዉም ቅርሳ ቅርስ አስፈላጊዉ ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል፣

ቀ/ በወረዳዉ ምክር ቤትና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፣

2. የወረዳ አስተዳዳር ም/ቤት አባላት በመንግሥታዊ ሥልጣናቸዉ ለሚፈጽሙት ተግባርና ለሚያሳልፋት ዉሣኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

## አንቀጽ 94

## ስለ ወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና

## የሥራ ዘመን

1. የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ በወረዳ ምክር ቤት ምርጫ አሸናፊ በሆነዉና በምክር ቤቱ ዉስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል፣

www.abyssinialaw.com

2. በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የወረዳዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፣

## አንቀጽ 95

## የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለወረዳዉ ምክር ቤትና ለዞን አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ የተሾመበት ወረዳ ተጠሪ፣ የአስተዳደሩ የሥራ መሪና የአስተዳዳር ም/ቤቱ ሰብሳቢ ነዉ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪዉ፣

   ሀ/ የወረዳዉን አስተዳደር ይወክላል፣

   ለ/ የወረዳን አስተዳደር ምክር ቤት ይሰበስባል፤ ይመራል፣

   ሐ/ የፌዴራሉና የክልሉ ሕገጋተ መንግሥታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በወረዳዉ ዉስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸዉን ያረጋግጣል:

   መ/ ምክትል አስተዳዳሪዉን ጨምሮ የወረዳዉን አስተዳደር ም/ቤት አባላት ሹመት ለወረዳዉ ም/ቤት አቀርቦ ያስፀድቃል። ምክትል አስተዳዳሪዉ የም/ቤት አባል መሆን አለበት።

   ሠ/ የወረዳ አስተዳደሩን ልዩልዩ ተቋማትና በሥሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል

   ረ/ የወረዳዉ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕግራሞች እና እቅዶች ወቅቱን ጠብቀዉ መዘጋጀታቸዉን ይቆጣጠራል፣ ተግባራዊነታቸዉንም ይከታተላል፣

   ሰ/ የወረዳዉ ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ሕግና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

www.abyssinialaw.com

ሸ/ ለወረዳዉ አስተዳደር ምክር ቤት፣ ለወረዳዉ ምክር ቤትና ለበላዩ የአስተዳደር አካላት በየጊዜዉ ሪፖርት ያቀርባል፣

ቀ/ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪዉ የወረዳዉን ምክር ቤት ምሥራች ጉባኤ ይጠራል፣

በ/ በወረዳዉ ምክር ቤትና በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል::

## አንቀጽ 96
## የወረዳ ምክትል አስተዳደሪ ሥልጣንና ተግባር እና የሥራ ዘመን

የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ በወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ አቅራቢነት ሹመቱ በወረዳዉ ምክር ቤት የሚፀድቅ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1 በዋና አስተዳዳሪዉና በወረዳዉ አስተዳደር ም/ቤት ተለይተዉ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል፣

2 ዋና አስተዳዳሪዉ በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣

3. ምክትል አስተዳዳሪዉ ተጠሪነቱ ለወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪና ለአስተዳደር ም/ቤቱ ነዉ::

4. የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የወረዳዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመንይሆናል::

## አንቀጽ 97
## የዋና አስተዳዳሪዉ ጽ/ቤት

1. የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪዉ የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል፣

2. የዋና አስተዳዳዉ ጽ/ቤት የወረዳዉ አስተዳዳር ም/ቤት ጽ/ቤት በመሆን ጭምር ሊያገለግል ይችላል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## ስለ ቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀጽ 98
### አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻ መንግሥታዊ የአስተዳደር እርከን ሲሆን በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ለታቀፈበት የከተማና ወይም የወረዳ አስተዳደር ነዉ::

2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል::
   ሀ/ የቀበሌ ምክር ቤት፣
   ለ/ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤትና
   ሐ/ የማህበራዊ ፍርድ ቤት፣

### አንቀጽ 99
### ስለቀበሌ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ አስተዳደር በተደራጀበት አካባቢ የኢካኖሚያዊና ማህበራዊ ዕቅዶችን የማዉጣትና መመሪያዎችን የማዘጋጀት፣ በሥራ ላይ የማዋልና እንዲሁም የመወሰን፣ ሥልጣን አለዉ::

2. እያንዳንዱ የቀበሌ አስተዳደር ራሱን የማስተዳደር፣ አካባቢዉን የማልማትና በዉስጣዊ ጉዳዮቹ ላይ ዉሣኔ የመስጠት መብትና ሥልጣን ይኖረዋል::

### አንቀጽ 100
### ስለቀበሌ ምክር ቤት

1. የቀበሌ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የቀበሌዉ ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተቋቁሟል::

www.abyssinialaw.com

2. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ።

3. የምክር ቤቱ አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ነው፣

4. የቀበሌ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳ ምክር ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ 101
## የቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የወረዳው ምክር ቤትና የወረዳው ምክር ቤት በየጊዜው የሚያወጧቸው እቅዶችና መመሪያዎች በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

2. የበላዩ የሆኑት የአስተዳደር አካላት ከሚያወጧቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች መመሪያዎች ጋር በማይቃረን መንገድ የአካባቢ ማህበራዊ ጉዳይ መመሪያዎችን አዉጥቶ በቀበሌ ዉስጥ በሥራ ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል።

3. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የቀበሌዉን አፈ ጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔና አስተዳዳሪ በምርጫ ይሰይማል፣ የቀበሌዉን የአስተዳደር ምክር ቤት ያደራጃል፣

4. የነዋሪዉን ሕዝብ ትችትና አስተያየት መሠረት በማድረግ በቀበሌ አስተዳዳሪ ተመርጠዉ የሚቀርቡለትን የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ይሾማል።

5. የበላዩ በሆኑ የአስተዳደር አካላት የሚሰጡትን የማህበራዊ፣የኢኮኖሚያዊ፣ ልማትና አስተዳደራዊ እቅዶችና ፕሮግራሞችን ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ የሚዉሉበትን ዝርዝር የሥራ አፈፃፀም መርሃ ግብር ያወጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

6. ለሚመለከተው ቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ የሚጠቅሙ ሌሎች ተጨማሪ እዕዶችን ያወጣል፣ ተግባራዊነታቸዉንም በቅርበት ይከታተላል፣

www.abyssinialaw.com

7. የቀበሌዉን ነዋሪ ሕዝብ ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣ የተፈጥሮ ሀብትን ልማትና እንክብካቤ ሥራ በቅርበት ይከታተላል፣

8. የቀበሌዉ ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት መጠበቁንና ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፣

9. የቀበሌዉን አስተዳዳሪ ምክትል አስተዳዳሪ ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈፃሚዉን አካል አሠራር ይመረምራል::

## አንቀጽ 102

## ስለ ቀበሌ ምክር ቤት አመራር

1. የቀበሌ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት የሚኖረዉ ሆኖ ከአባላቱ መካከል የሚመረጡ አንድ አፈ ጉባኤ እና አንድ ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

2. አፈ ጉባኤዉ ተጠሪነቱ ለቀበሌዉ ምክር ቤት ሆኖ ምክር ቤቱን በወቅቱ ይሰበስባል፣ ይመራል፣ አጀንዳዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ቃለ ጉባዔዎች መያዛቸዉንና ሠነዶች መጠበቃቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

3. ምክትል አፈ ጉባዔዉ ተጠሪነቱ ለአፈ ጉኤዉና ለቀበሌ ም/ቤት ሆኖ:-

   ሀ/ በአፈ ጉባኤዉ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል፣

   ለ/ አፈ ጉባኤዉ በማይገኝበት ወይም ሥራን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል::

## አንቀጽ 103

## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌዉ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባዉን በወር አንድ ጊዜ ያካሄዳል::

2. ከምክር ቤት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል:: የምክር ቤቱ ዉሣኔ በስብሰባዉ ላይ በተገኙት የምክር ቤት አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል::

www.abyssinialaw.com

3. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል:: የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል:: የቀድሞዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ዉስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራዉን ይጀምራል::

4. የቀበሌዉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል:: ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይደረግበት ወቅት አፈ ጉባዔዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል:: የቀበሌ አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ ጉባዔዉ የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት::

## አንቀጽ 104

## ስለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት

1. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የቀበሌዉ አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በቀበሌዉ ምክር ቤት አማካኝነት በተጨማሪ ተመርጠዉ የሚሰየሙ ሆነዉ በቀበሌዉ ዉስጥ ከሚገኙ የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ የመንግሥት ተቋማት ሠራተኞች በአባልነት የሚገኙበትና የበላዩ በሆኑት የአስተዳዳር አካላት ለሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የመጨረሻ አስፈፃሚ አካል ነዉ::

2. የቀበሌዉ አስተዳዳር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌ አስተዳዳሪ፣ ለመረጠው የቀበሌ ምክር ቤትና እንደሁኔታው ቀበሌ ለታቀፈበት ከተማ አስተዳዳርና ወይም ለወረዳዉ አስተዳደር ይሆናል::

3. የቀበሌ አስተዳዳር ምክር ቤት አባላት በግልና በወል የቀበሌዉን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ::

4. የቀበሌ አስተዳዳር ምክር ቤት አባላት በጋራ ሥልጣናቸዉ ለሚያሳልፉ ዉሳኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ የሆነ ኃላፊነት አለባቸዉ::

## አንቀጽ 105

## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

www.abyssinialaw.com

1. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 104 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ/ የቀበሌዉ ምክር ቤት የሚነድፋቸዉን የልማት እቅዶችና ፕሮግራሞች በቀበሌዉ ዉስጥ በሥራ ላይ ያዉላል፣ የራሱን ዝርዝር የልማት እቅዶች ይነድፋል፣ ለቀበሌዉ ምክር ቤት እያቀረበ ያስፀድል፣

ለ/ በቀበሌዉ ዉስጥ የሚካሄዱ የማህበራዊ አገልግሎት እቅዶች በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ/ የገጠር ልማትን ያፋጥናል፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ እንክብካቤና ልማት ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ሕዝቡን ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣ ያስተባብራል፡

መ/ የቀበሌዉ ሠላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣

ሠ/ በአካባቢ ለሚገኙ ቅርሳ ቅርሶች ተገቢዉን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፣ በጥቅም ላይ ስለሚዉሉበት መንገድም የበላዩ ለሆኑት አካላት ያሳዉቃል፣

ረ/ የሥራ እንቅስቃሴዉን በሚመለከት ለቀበሌዉ ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖርት ያደርጋል።

ሰ/ በቀበሌ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል።

2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ዝርዝር የሥራ እቅዶቹን የሚነድፈዉንና አፈፃፀማቸዉን የሚከታተለዉም ሆነ የሚገመግመዉ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜዉ እየተገናኘ ይሆናል።

## አንቀጽ 106

## ስለ ቀበሌ አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌ አስተዳዳሪ በቀበሌ ምክር ቤት ምርጫ አሸናፊ በሆነዉና በምክር ቤቱ ዉስጥ አብላ መቀመጫ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክር ቤቱ አካላት መካከል ተመርጦ ይሰየማል።

www.abyssinialaw.com

2. በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል::

## አንቀጽ 107

## የቀበሌ አስተዳደሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌው አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና እንደሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳዳር ሆኖ የቀበሌው ተጠሪ፣ የአስተዳዳሩ ሥራ መሪና የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ነው::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

   ሀ/ የቀበሌዉን የአስተዳዳር ምክር ቤት ይሰበስባል፣ ይመራል፣

   ለ/ የበላዩ በሆኑት የአስተዳዳር አካላት የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና እቀዶች ተቀብሎ በቀበሌው ዉስጥ በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

   ሐ/ ምክትል አስተዳዳሪዉን ጨምሮ የቀበሌዉን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለቀበሌ ም/ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፣

   መ/ የነዋሪዉን ሕዝብ አስተያየት መሠረት አድርጎ በቀበሌው አስተዳዳር ምክር ቤት አማካኝነት እንዲጣራ ካደረገ በኋላ የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞች ዝርዝር ለቀበሌ ምክር ቤት አቀርቦ ያሾማል::

   ሠ/ ለቀበሌው ምክር ቤት፣ ለነዋሪው ሕዝብ እንደአስፈላጊነቱ ቀበሌ ለታቀፈበት ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳዳር በየጊዜው የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፣

   ረ/ በቀበሌው አስተዳዳር ም/ቤት፣ በቀበሌው ምክር ቤትና እንደሁኔታው በሚመለከተው ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳደር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 108
## የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር የሥራ ዘመን

የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ በቀበሌው አስተዳዳሪ ተመርጦ ሹመቱ በቀበሌው ም/ቤት የሚፀድቅ ሆኖ፣

1. በቀበሌው አስተዳደር ም/ቤት እና በአስተዳዳሪው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
2. የቀበሌው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣
3. የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለአስተዳደር ም/ቤቱ ነው።
4. የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 109
## ስለቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት

የቀበሌ አስተዳደር የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል።

ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 110
## የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የቀበሌው ማህበራዊ የዳኝነት አካል ሆኖ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር በተደነገገው መሠረት ተመርጠው የሚሾሙ ይሆናሉ።

www.abyssinialaw.com

3. የማኅበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥራ ዘመን የቀበሌ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል። ዝርዝሩ በህግ ይደነገጋል።

## ምዕርፍ አሥራ ሁለት

## የክልሉ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች

### አንቀጽ 111

### ዓላማዎች

1. ማንኛውም የመንግሥት አካል የፌዴራሉንና የክልሉን ሕግጋተ መንግሥታት፣ ሌሎች ሕጎችና ፖሊሲዎች በሥራ ላይ ሲያዉል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት።

2. በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ " መንግሥት " ማለት የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ማለት ነዉ።

### አንቀጽ 112

### የፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

1. የሀገሪቱን የፈጣን የልማት ራዕይ እዉን ለማደረግ ከሙስና የፀዳ፣ ቀልጣፋ፣ ዉጤታማ፣ ግልጽነት የተላበሰና ለሕዝብና ለሕግ ተጠያቂ የሆነ መልካም አስተዳደር ይመሰርታል። መንግሥት በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሁሉም ደረጃዎች ራሳቸዉን በራሳቸዉ የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

2. መንግሥት በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት የማክበርና የማስከበር እና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸዉ እኩልነትን፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን ለማጠናከር ግዴታ አለበት።

### አንቀጽ 113

### የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

1. የጋምቤላ ክልል ሥነ-ምህዳር (በቂ ዝናብ ለም መሬት) መሠረት ደረገ፣ የክልሉን ተነጻጻሪ ብልጫዎች ላይ ያተኮረ፣ ፈጣን የተሳሰረና በገበያ የሚመራ የኢኮኖሚ

www.abyssinialaw.com

እንቅስቃሴ ያደርጋል:: ለዚሁም የሕዝቡ፣ የባለሃብቶችና የራሱ የመንግሥት የልማት ኃይሎችን በቅንጅት ይመራል:: ከአገሪቱ የገበያ ማዕከላት ለማገናኘት አቅም በፈቀደ መጠን የመሠረተ ልማት ዝርጋታን ያፋጥናል:: መንግሥት ሁሉንም የክልሉ ነዋሪዎች ባላቸዉ እዉቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት::

2. የክልሉ ነዋሪዎች የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸዉ ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት::

3. የተፈጥሮና ሰዉ ሠራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋዉ ሲደርስም ለተጐጂዉ ሕዝብ እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት::

4. መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታዉ ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅም እንዲዉሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት::

5. የክልሉ የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ ሕዝቡ እንዲሳተፍ ማድረግ አለበት:: የሕዝቡን የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት::

6. መንግሥት የሕዝቡን እዉቀት፣ ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት:: ሕዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረዉ ማድረግ አለበት:: ስለሆነም ሕዝቡ ዕቅዶችና ፖሊሲዎችን በመደገፍ ብቻ ሳይሆን በማስፈፀምና በመገምገም መሳተፍ አለበት::

7. መንግሥት በኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት::

8. የመንግሥት ሠራተኛዉን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 114
## ማህበራዊ ነክ ዓላማዎች

1. የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህረት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ዉሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና ማህበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸዉ ያደርጋል።

2. ትምህርት ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ከባህላዊ ተጽዕዎች ነፃ በሆነ መንገድ ይካሄዳል።

## አንቀጽ 115
## ባህል ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት መሠረታዊ መብቶችና ሰብዓዊ ክብርን እንዲሁም ዲሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጐለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃለፊነት አለበት።

2. በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ግዴታ ነዉ።

3. የክልሉ መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነ ጥበብን፣ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት።

4. የክልሉ መንግሥት ወጣቱን ትዉልድ የመንከባከብ፣ በተሟላ ሥነ ምግባር የማነጽ፣ በአካልም ሆነ በአእምሮ ጠንክሮ ኃላፊነት የሚሸከም፣ ሀገሩን የሚወድና ለወገኑ የሚቆረቆር ብቁና በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ያላሰለሰ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 116
## የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረዉ የመጣር ኃላፊነት አለበት።

2. ማንኛዉም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢዉን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።

3. የሕዝብንና የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና በሥራ ላይ በሚዉልበት ጊዜ የሚመለከተዉን ሕዝብ ሃሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት።

4. መንግሥትና የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸዉን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸዉ።

# ምዕራፍ አሥራ ሶስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 117
## የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1. በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ና በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2.17 በተደነገገዉ መሠረት ማናቸዉም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 8 ሥር በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት ያስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አዉጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል።

2. የክልሉ መስተደድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉን አዉጥቶ በሥራ ላይ ባዋለ በአሥራ አምስት ቀናት ዉስጥ አፈ ጉባኤዉ የክልሉን ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማሳወቅና የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉን ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማጽደቅ አለበት።

www.abyssinialaw.com

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣዉን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በክልሉ ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘ በሥራ ላይ ሊቆይ የሚችለዉ ለስስት ወራት ብቻ ይሆናል:: ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉ በየአራት ወሩ እንዲታደስ ለማድረግ ይችላል::

4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና የክልሉ ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አማካኝነት የሚያወጧቸዉ ደንቦችና የሚወስዷቸዉ እርምጃዎች በማናቸዉም ረገድ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 16፣ አንቀጽ 17፣ አንቀጽ 19/1 እና /2/፣ አንቀጽ 22/1 /፣ አንቀጽ 25/1 /፣ አንቀጽ 26፣ አንቀጽ 28/1/ እና አንቀጽ 49/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ሥር የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸዉም::

## አንቀጽ 118

## የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

1. በክልሉ ዉስጥ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና በሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸዉና ሰባት አባላት ያሉት አስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ ማቋቋም ይችላል::
ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉ በክልል ምክር ቤት በሚፀድቅበት ጊዜ ይቋቋማል::

2. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

   ሀ/ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሰሩ ግለሰቦች ቢኖሩ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለጽ፣

   ለ/ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸዉም ረገድ ኢሰብአዊ አለመሆናቸዉን መከታተልና መቆጣጠር፣

www.abyssinialaw.com

ሐ/ ማናቸዉም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ ኢሰብአዊ መሆኑን ሲያምንበት ርዕሰ መስተረዳድሩ ወይም መስተዳድር ምክር ቤቱ እርምጃዉን እንዲያስተካክል ሃሳብ መስጠት፣

መ/ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም እርምጃዎች ኢሰብአዊ ድርጊት የፈፀሙ ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

ሠ/ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም እንዲቀጥል ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለዉን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ፣

3. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተልዕኮዉን እንዳጠናቀቀ የሚፈርስ ይሆናል::

## አንቀጽ 119

## የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር በርዕሰ መስተደድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ:: ተጠሪነታቸዉም ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል::

2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉ መንግሥት ተቋማትና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሣቦችን በመቆጣጠር በክልል ምክር ቤት የተመደበዉ ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ ዉስጥ እንዲሰሩ ለተወሰኑት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል::

3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል::

4. የዋናዉ ኦዲተር መ/ቤት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 120
## የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሣብ ስለማመንጨት

የዚህ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሣብ፣

ሀ/ በክልል ምክር ቤት አባላት አንድ ሶስተኛ ጠያቂ ወይም፣

ለ/ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ያብላጫ ዉሣኔ ወይም፣

ሐ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የብሔረሰብ ዞንና የብሔረሰብ ልዩ ወረዳ ምክር ቤት በአንድ ሶስተኛዎቹ ጥያቄ ወይም፣

መ/ በክልሉ ዉስጥ የሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛዎቹ ጥያቄ ወይም፣

ሠ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የቀበሌ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛዉ ጥያቄ ለዉይይትና ለዉሣኔ የሕገ መንግሥቱ መሻሻል ጉዳይ ለሚመለከታቸዉ ክፍሎች ይቀርባል።

## አንቀጽ 121
## ሕገ መንግሥቱን ስለማሻሻል

1. የዚህ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሁለትና ምዕራፍ ሶስት ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሁለትና ሶስት ሲሻሻሉ ብቻ ነዉ። በዚህ መሠረት የሚደረገዉ ማሻሻያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌ መሠረት ይፀድቃል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከተዘረዘሩት ዉጪ ያሉት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለዉ አኳኋን ብቻ ይሆናል።

ሀ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአብላጫ ድምጽ ሲያፀድቁትና፣

www.abyssinialaw.com

ለ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የብሔረሰብ ዞን ወይም የብሔረሰብ ልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአብላጫ ድምጽ ሲያፀድቁትና፣

ሐ/ የክልሉ ምክር ቤት አባላት በሶስት አራተኛዉ ድምፅ ሲያፀድቁት ነዉ::

3. ይህ ንዑስ አንቀጽና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የቀረበዉን ማሻሻያ

ሀ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲያፀድቁትና፣

ለ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የብሔረሰብ ዞን ወይም የብሔረሰብ ልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲያፀድቁትና፣

ሐ/ የክልሉ ምክር ቤት አባላት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀድቁት ነዉ::

## አንቀጽ 122
## ነባር ሕጎች ስለመሥራታቸዉ

በብሔራዊ ክልሉ ዉስጥ እስካሁን ድረስ ፀንተዉ የሚሰራባቸዉ ነባር ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተሻሽለው ከወጣዉ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::

## አንቀጽ 123
## የመጨረሻ ሕጋዊ ዕቅዉና ስላለዉ ቅጂ

የዚህ ሕገ መንግሥት የአማርኛ ቅጂ የመጨረሻዉ ሕጋዊ ዕዉቅና ያለዉ ሠነድ ነዉ::